# ፈጣን ነው ባቡሩ

ለሚ ዋቄ 03-14-18

ከሃያ ዓመታት በፊት የነበሩት የሃገሪቱ ከተሞች አውራ መንገድ ላይ ያሉት ጭምር፣ የሽጉጥ ድምጽ እንደሚጠብቅ የሩጫ ተወዳዳሪ ዘመው በአፍጢማቸው ሊተከሉ የተቃረቡ መደዴ የጭቃ ቤት የተደረደሩባቸው መንደሮች ነበሩ። እነዚህ ተያይዘው የተደረደሩ የአፈር ቤቶች አብዛኞቹ የጠላና አረቄ መሸታ ቤቶች ናቸው፤ ደጃፋቸው ላይ እንጨት ላይ በተሰካ ጣሳ ጠጪያቸውን የሚጣሩ ጨለማ መሸታ ቤቶች። መሃከላቸው አንድ ሁለት ሻይ ቤቶች ይኖራሉ። በዘይት የጠቆረ መስታወት ባለው ባንኮኒያቸው ውስጥ ጮርናቄ አጭቀው፣ ባነኮኒው ላይ ያደፈ ላስቲክ ለብሶ በተቀመጠ አሮጌ ትሪ የተከመረ ድንች ቅቅል አስቀምጠው ከተሜ ወጣቶችን የሚያስተናግዱ ሻይ ቤቶች። እነዚህ ሻይ ቤቶች ቀኑን ሙሉ ከሚሰራጨው የትምህርት በሬዲዮ ጣቢያ የሚለቀቀውን ሙዚቃ፣ ከሶስተኛ ክፍል የእንግሊዘኛ ቀንቋ፣ ከአምስተኛ ክፍል አማርኛ፣ ከስድስተኛ ክፍል የህብረት . . .ትምህርት ጋር አዋህደው የሚየስኮሞክሙ ብቸኛ የወጣቶች "መዝናኛዎች" ናቸው።

ከተሞቹ በአዘቦት ቀናት ከመሸታ ቤት ውጭ ይህ ነው የሚባል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አይታይባቸውም። እርግጥ የገበያ ቀን አርሶ አደሮች፣ ሴቶቹ  በጀርባቸው አዝለው፣ ወንዶቹ በአህያ ጭነው በሚያቀርቧቸው ምርቶች፣ እየነዱ በሚያመጧቸው ከብቶች ሞቅ ይላሉ።  እነዚህን አፈር የሚመስሉ ከተሞች የገበያ ቀን እንደነገሩ የሚያሞቋቸው አርሶ አደሮች ለእግራቸው ጫማ የሌላቸው፣ የተጣፈ የለበሱ፣ በአጠገባቸው አልፎ አልፎ አቧራ አልብሰዋቸው የሚያልፉትን መኪኖች፤ ጽዱ የለበሱ፣ ጫማ የተጫሙ ከተሜዎች እንደትንግር የሚመለከቱ ምስኪኖች ናቸው።

አይነ ግብ ከተሜዎች የመሸታ ቤት ኮማሪቶች፣ የገበያ ቀን የሚከፈቱ ሱቆች ነጋዴዎችና ልብስ ሰፊዎች ናቸው። በሁሉም ከተሞች የማይጠፉት የግብርና ልማት ወኪል ጽህፈት ቤት ሰራተኞች፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን፣ ፖሊሶች ወዘተም የከተሞች ፈርጦች ነበሩ። ከተሞቹ ከእህል ወፍጮ ቤት ያለፈ የሞተር ድምጽ አይሰማባቸውም። ምንም አይነት ዎርክ ሾፕ ወይም ፋብሪካ የላቸውም። ፉርኖ ዳቦ በአውራጃ ከተሞች ብቻ ነው የሚገኘው። ኬክ  ደግሞ አዲስ አበባ ብቻ።

ይህ በግርድፉ የገለጽኩት ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት የነበረ የሃገራችን ከተሞች ገጽታ አዲስ አበባ ዙሪያ ያሉትን ሰበታ፣ ቡራዩ፣ ሱሉልታ፣ ሰንዳፋ፣ ዱከም ያጠቃልላል። አሁን እነዚያን ከተሞች የምናውቃቸው እድሜያችን ከሰላሳዎቹ አጋማሽ በላይ ያለን ነን። አሁን የሃገሪቱ ከተሞች ገጽታ በእጅጉ ተቀይሯል።

በመንገድ ግራ ቀኝ ተያይዘው ተደርድረው የነበሩት የዘመሙ መሸታ ቤቶች እንደየከተሞቹ ሁኔታ በባለሁለት፣ ሶስትና አራት ፎቅ ህንጻዎች እየተቀየሩ ነው። ቁጥራቸውና የጥራት ደረጃቸው ይለያይ እንጂ፣ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የሃገሪቱ ከተሞች የተሟላ ሊባል የሚችል የመኝታ፣ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎች ተገንብተዋል። ድሮ አዲስ አበባ ምናልባት የክፍለሃገር ዋና ከተሞች ላይ ብቻ የሚገኙ ሸቀጦችን የሚሸጡ ትላልቅ መደብሮች በሁሉም የሃገሪቱ ከተሞች አሉ። አሁን እቃ ለመሸመት የዞን፣ የክክል ከተሞች መውጣት ወይም አዲስ አበባ መምጣት አያስፈልግም። ሁሉም አይነት ሸቀጥ በሚፈለገው መጠንና ጥራት በሁሉም ከተሞች ይገኛል።

ድሮ አዲስ አበባና የክፍለ ሃገር ዋና ከተማ ብቻ ይገኙ የነበሩ የግል ክሊኒኮች አሁን በሁሉም የሃገሪቱ ከተሞች አገልግሎት ይሰጣሉ። ደሮ ብርቅ የነበሩት ጽዱ ኬክ ቤቶች (ካፍቴሪያዎች) አሁን የሌሉበት ቦታ የለም። ሁሉም ከተሞች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አላቸው። ሁሉም ከተሞች የመንግስት የጤና አገልግሎት ተቋማት አላቸው። በርካታ ከተሞች የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አላቸው። የመቆራረጥ ችግር መኖሩ ሳይዘነጋ ሁሉም የሃገሪቱ ከተሞች የኤሌትሪክ ሃይል ተጠቃሚዎች ናቸው። የውሃ ስርጭትም ችግር መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብዙዎቹ የሃገሪቱ ከተሞች ቢያንስ የውሃ ቧምቧ ተዘርግቶላቸዋል።

በማምረቻ ዘርፍም ድሮ ከእህል ወፍጮ ያለፈ የሞተር ድምጽ የማይሰማባቸው ከተሞች አሁን በርካታ የብረታብረትና የእንጨት ስራ ዎርክሾፖች አሉዋቸው። ፋብሪካዎችም ብርቅ አይደሉም። በኦሮሚያ ብቻ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ከ1 ሺህ በላይ የተለያየ ምርት የሚያመርቱ ቀላል፣ መካከለኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች ተገንብተዋል። በስንዴ ምርት የሚታወቀው ሆኖም ፉርኖ ዳቦ ብርቅ የነበረባቸው የባሌ ከተሞች ዛሬ ለሃገሪቱ ፉርኖ ዱቄት የሚያከፋፍሉ በርካታ ዱቄት ፋብሪካዎች ተቋቁሞባቸዋል። በአዲስ አበባ ከተማ የታየውን እድገት በአጭር የጋዜጣ ጽሁፍ ገልጾ መጨረስ ስለማይቻል እተወዋለሁ። በደፈናው እጅግ ድንቅ የሚያሰኝ እድገት ተመዝግቧል። አዲስ አበባ ባለፉት ሃያ ዓመታት ከዚያ በፊት በነበረው የመቶ አመት እድሜዋ ካስመዘገበችው እድገት በእጅጉ የሚበልጥ እድገት አስመዝግባለች።

ይህ የከተሞች እድገት ከየት ይሆን የመጣው? ድንገት ከሰማይ አልወረደም። ወይም በስጦታ የተገኘ አይደለም። በሃገሪቱ ውስጥ የተፈጠረ ተጨማሪ ሃብት የወለደው ነው።

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በስልጣን ላይ የቆየው መንግስት ገጠርና ግብርና ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ ልማት ፓሊሲ ነው የተከተለው። ይህን ያደረገው በተጨባጭ ያለው ሊለማና ሃገራዊ የካፒታል ክምችት ሊፈጥር የሚችለው ሃብት ገጠርና ግብርና ላይ ያለ በመሆኑ ነው። ሌላ የልማት መነሻ አማራጭ አልነበረም።

ይህ ፖሊሲ፣ ኑሮው በአነስተኛ ማሳ ላይ የተመሰረተውን ከአጠቃላይ የሃገሪቱ ህዝብ ከ80 በመቶ በላይ የሚሸፍነውን አርሶ አደር ምርታማነት በማሳደግ በምግብ ራሱን ማስቻል የመጀመሪያው ግቡ አድርጎ ነበር የተነሳው። ይህን በአመዛኙ ማሳካት ተችሏል። በተለይ በሃገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ ሃገሪቱ በምግብ ራስዋን ችላለች። እርግጥ አሁንም በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ፍላጎት ያልተሟላበት ሁኔታ አለ። ይህ ለወደፊትም ቢሆን በቀላሉ አይጠፋም። በኢኮኖሚ የመጨረሻው የእድገት ደረጃም ላይ የደረሱ የበለጸጉ ሃገራትም በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ያላረጋገጡበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይሁን እንጂ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጡ ሰዎችን ለረሃብ አያጋልጥም። በእርዳታም ይሁን በምግብ ለስራ ፕሮግራም በልተው የሚያድሩበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።

ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ ሃገሪቱን የመታትና እስካሁንም ተጽእኖው ያላበቃው ከ10 ሚሊየን በላይ ዜጎችን ለምግብ እጥረት ያጋለጠውን አስከፊ ድርቅ በአብዛኛው በራስ አቅም መቋቋም መቻሉ ሃገሪቱ በምግብ ራሷን በመቻል የደረሰችበትን ደረጃ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በዚህ አስከፊ ድርቅ ምክንያት አንድም ዜጋ ለረሃብ አልተጋለጠም፤ ከመኖሪያው አልተፈናቀለም። ከሁለት አስርት ተኩል ዓመታት በፊት የተከሰቱት ድርቆች ግን በሚሊየን የሚቀጠሩ ዜጎችን ለችጋር አጋልጠው ለቁጥር የሚያታክቱትን እንደቅጠል አርግፈዋል።

በርካታ አርሶ አደሮች ምርታማነታቸው ከዓመት ዓመት እያደገ በመምጣቱ አሁን በምግብ ራሳቸውን ከመቻል አልፈው ሃብት ወደማፍራት እየተሸጋገሩ ይገኛሉ። አርሶ አደሩ ማህበረሰብ ከእጅ ወደ አፍ ብቻ የነበረው ገቢው በማደጉ ኑሮው ተቀይሯል። ድሮ በአርሶ አደሩ መንደር ብርቅ የነበሩ የቆርቆሮ ክዳን ቤቶች አሁን የተለመዱ ሆነዋል። አርሶ አደሩ አሁን ደረጃውን የጠበቀ መኖሪያ ቤት ውስጥ መኖር ጀምሯል። የከብት በረቱን ከመኖሪያ ቤቱ ለይቷል። የጢስ ቤቱንም እንዲሁ። የተሟላ የቤት እቃ አለው።

በቂና ጽዱ የሌሊትና የቀን ልብስ አለው። ጫማ መጫማት አሁን ለአርሶ አደሩ ብርቅ አይደለም። አሁን በአንድ የአርሶ አደር አባ ወራ ቢያንስ አንድ ተንቀሳቃሽ ስልክ አለ። አብዛኛው የአርሶ አደር መኖሪያ መንደሮች ከኤሌትሪክ መስመር ውጭ ቢሆኑም፣ አሁን አሁን አርሶ አደሩ በጸሃይ የኤሌትሪክ ሃይል መጠቀም እየተለማመደ መጥቷል። ከኤሌትሪክ ሃይል ውጭ መኖር የሚያዳግተው ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ ብቻ እጅግ ከፍተኛ ሃብት ያካበቱ አርሶ አደሮች ቁጥር ቀላል አይደለም። አሁን በአንድ የአርሶ አደር ቀበሌ አራት አምስት የጭነትና የህዝብ ማመላለሻ ከባድ መኪና ያላቸውን አርሶ አደሮች መመለከት የተለመደ ነው። የቤት መኪና ያላቸውም አርሶ አደሮች አሉ። በከተማ የሚከራዩ ተላልቅ ህንጻዎች ያስገነቡ፣ በአካባቢያቸው የእህል ወፍጮ ያቆሙ በርካታ አርሶ አደሮች ተፈጥረዋል። በሚሊየን የሚለካ ሃብት አፍርተው ወደሃገር በቀል ኢንቨስተርነት የተሸጋገሩትም በርካቶች ናቸው።

በዚህ ሁኔታ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን  ህዝብ የሚሸፍነው አርሶ አደር ገቢ ማደጉ በሃገሪቱ ትልቅ የገበያ አቅም ፈጥሯል። ይህ የገበያ አቅም የአምራች፣ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ዘርፎችን አነቃቅቷል። እነዚህ የኢኮኖሚ ዘርፎች በሃገሪቱ በተፈጠረው ከፍተኛ የገበያ አቅም ምክንያት ትርፋቸው አድጓል። በሃገሪቱ ከተሞች ቀደም ሲል ያልነበሩት ህንጻዎች፣ ሆቴሎች፣ ትላልቅ መደብሮች፣ ፋብሪካዎች . . . የተገነቡት፣ በአበአርሶ አደሩ ገቢ ማደግ ከተፈጠረው ከፍተኛ ገበያ አትርፈው ሃብት ማከማቸት በቻሉ ነጋዴዎች ነው። ገጠሩና ከተማው በዚህ ሁኔታ ተደጋግፈው አደገዋል፤ ይህ እድገት አሁንም እንደቀጠለ ነው። በዚህ ሁኔታ በገጠርና በከተማ የተፈጠረው ከፍተኛ የገበያ አቅም ሃገሪቱ በስራ ላይ ካዋለችው ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ጋር ተዳምሮ ከሃገር ውስጥ ባለሃብት በተጨማሪ በርካታ የውጭ ባለሃብቶችን መሳብ አስችሏል። በዚህ ሁኔታ ያደጉት ከተሞች በእድገታቸው ልክ የስራ እድልም ፈጥረዋል።

መንግስት ከፍተኛ በጀት በመመደብ በተለይ በመንገድ፣ በሃይልና በቴሌ ኮሚዩኒኬሽን መሰረተ ልማት ማስፋፋት ላይ ያከናወነው ተግባር ደግሞ እድገቱን አቀላጭፎታል። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት በትምህርትና በጤና ዘርፍ ልማት ከፍተኛ ሃብት አፍስሶ የአገልግሎት ዘርፎቹ በከፍተኛ መጠን እንዲያድጉ አድርጓል። አሁን በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች ወጣቶች የትምህርት እድል ማግኘት ችለዋል። በመላ ሃገሪቱ በሺህ የሚቆጠሩ የሞያና የቴክኒክ ኮሌጆች ተቋቁመው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። አሁን በሃገሪቱ አገልግሎት በሚሰጡ 40 ያህል ዩኒቨርሲቲዎች በመቶ ሺህ የሚቀጠሩ ወጣቶች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ።

ሃገሪቱ በዚህ ሁኔታ ባለፉ አንድ ተኩል አስርት ዓመታት ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ችላለች። ይህ እድገት በዚህ ከቀጠለ ሃገሪቱ ከ7 ዓመታት በኋላ በ2017 ዓ/ም ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ደረጃ ላይ ትደርሳለች። ይህ ገለልተኛ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚና የገንዘብ ተቋማት የመሰከሩለት ተጨባጭ እውነት ነው።

ይህ የማያቋርጥ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ባቡር ቀደም ሲል ከነበረው የድህነት ቀለበት ኡደት ዘመን የተለየ ሁኔታ ፈጥሯል። በድህነት ቀለበት ኡደት ውስጥ የሚኖር ህዝብ ከእለት ጉርሱና ከአመት ልብሱ ያለፈ ፍላጎት የለውም። እነዚህን ካሟላ "ተመስገን" ብሎ ከድህነት ጋር ተስማምቶ መኖር ይችላል። በፈጣን እድገት ውስጥ ያለ ህዝብ ግን ፍላጎቱም ያለማቋረጥ ከእድገቱ ጋር ይጨምራል። በእድገት ውስጥ ያለ ህዝብ *አምጣ* የሚል ብቻ ሳይሆን *ተጨማሪ አምጣ* የሚል ነው። የበጋ መንገድ ሲዘረጋ የኢኮኖሚና ማህበራዊው እንቅስቃሴ እድገቱ ስለማይቋረጥ አስራ ሁለቱንም ወራት ማገልገል የሚችል መንገድ ይፈልጋል። አስራ ሁለቱንም ወራት የሚያመለግል መንገድ ሲያገኝ፣ እንቅስቃሴውን የበለጠ በማቀላጠፍ በፍጥነት በማደግ ላይ ካለው እድገት ተጠቃሚ ለመሆን የአስፓልት መንገድ ይፈልጋል።

በፈጣን እድገት ውስጥ ያለ ህዝብ ለመብራት የሚሆን ኤሌትሪክ ሲያገኝ፣ በዚህ ረክቶ አይቆምም። ከፍተኛ ጉልበት ያለው ማሽን የሚያንቀሳቅስ የኤሌትሪክ ሃይል ይፈልጋል። ወንዝ ወርዶ ያገኝ የነበረውን ውሃ በመንደሩ ከተተከለ የቦኖ ውሃ ማግኘት ሲችል፣ ውሃ በየቤቱ እንዲገባለት ይፈልጋል። በየቤቱ ውሃ ሲገባለት እይተሻሻለ ከሚሄደው ኑሮው ጋር የውሃ ፍጆታው ስለሚለወጥ፣ በማያቋርጥ እድገት ላይ ያለው የማምረቻ፣ የኮንስትራክሽንና የአገልግሎት ዘርፍ የፍጆታ ውሃውን ስለሚሻማው የውሃ ስርጭት መጠኑ እንዲያድግ ይፈልጋል።

ጤና ጣቢያ ሲያገኝ፣ ሆስፒታል ይጠይቃል። የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ሲያገኝ፣ ሪፈራል ሆስፒታል ይጠይቃል። ሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት ሲያገኝ፤ ኮሌጅ ይጠይቃል። ኮሌጅ ሲያገኝ፣ ዩኒቨርሲቲ እንዲኖረው ይፈልጋል . . .። ፍላጎቱ አይቋረጥም። ተቀጣጠሎ በፍጥነት መጓዝ የጀመረን የኢኮኖሚ እድገት ማንም ሊገታው አይችልም። ባልታሰበ ሁኔታ የሚፈጠር የእርስ በርስ ግጭት ወይም ጦርነት ካልሆነ በስተቀር። በፍጥነት እያደገ ያለን የእድገት ጉዞው እንዲቀጥል የሚገፋው ህዝብ ራሱ ነው። የእድገቱ ቀጣይነት ጠባቂ ህዝብ ነው። የመንግስት ተግባር የእድገቱን ፍጥነትና ፍጥነቱ የሚጠይቀውን ተጨማሪ ፍላጎት አስቀድሞ ተንብዮ ይህን ማሟላት የሚያስችል ፖሊሲ ቀርጾ ተፈጻሚ ማደረግ ብቻ ነው። ይህን ማድረግ ካልቻለ ከህዝቡ የማያቋርጥ ፍላጎት ጋር ይላተማል።

በማያቋርጥ እድገት ላይ ያለ እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ ፍጥነቱን እየጨመረ ያለማቋረጥ ለመጓዝ ሞተሩን ባስነሳ ባቡር ሊመሰል ይችላል። ባቡሩ ስለማይቆም ሃዲዱ አስቀድሞ ሊዘረጋለት፣ ወይም ከስር ከስር ከጉዞው ፍጥነት ቀድሞ ሃዲድ ሊዘረጋለት ይገባል። ከፍጥነቱ መጨመር ጋር የሚጨምር የሃይል አቅርቦት ይፈልጋል። ይህ መሆን ካልቻለ ሃዲዱን ሊጠርግለት፣ ሃይል ሊያቀብለው ከፊቱ ከተሰየመው አካል ጋር ይላተማል። ይህ ከመሆኑ በፊት  የተሻለ ቅልጥፍና ባለው መቀየር ይኖርበታል፤ አለበለዚያ ፈጣኑ ባቡር ይጠራርገዋል። ታዲያ ሲጠራርገው ባቡሩም ተሳፋሪውም ዳግም ላይኖሩ ወይም ሊሰባበሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

አሁን ኢትየጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል። ፍጥነቱን እየጨመረ የሚጓዘው የኢኮኖሚ እድገት ባቡር ጉዞውን ጀምሯል። መንግስት ግን ጉዞውን ማስቀጠል እያቃተው ይመስላል። አሁን ህዝቡን እያስቆጣ ያለው አዳዲስ የልማት ጥያቄ፣ የልማት ፕሮጀክቶች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ የሚቀርብ ጥያቄ፣ በየወቅቱ እየጨመረ የመጣ የሰለጠነ የሰው ሃይል የስራ እድል ጥያቄ ወዘተ ከእድገቱ የመነጨ ነው። መንግስት ደግሞ እየተንቀራፈፈ ነው። ስልጣንን ለግል ኑሮ ማደላደያነት መጠቀም፤ ኪራይ ሰብሳቢነትና የመልካም አስተዳደር መጓደል፣ የአመራር ብቃት ማነስ ወዘተ የመንቀራፈፉ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው።

አሁን ፈጣኑ የእድገት ባቡር መንግስትንም ሃገሪቱንም ይዟት ገደል እንዳይገባ የሚያሰጋ ሁኔታ ላይ ነው ያለነው። እድገቱና የእድገት ተስፋው የመጥፋት አደጋን ከጎኑ አብቅሏል። አሁን መንታ መንገድ ላይ ነን። እናም መንግስት የፈጣኑን ባቡር ጉዞ ማስቀጠል፣ ወይም ሃላፊነቱን ማስቀጠል ለሚችል ማስረከብ ይጠበቅበታል።